# እናት አፍሪካና ልጆቿ !

**ይህ ጽሁፍ መታሰቢያነቱ የአዲሱ ብሩህ ዓለም በር ከፋች ለሆኑት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለክቡር ባራክ ኦባማ ይሆን ዘንድ በታላቅ አክብሮትና ትኅትና እጠይቃለሁ ።**

በአኅጉረ አፍሪካ ውስጥ ዘመናት ያላስወገዱት ፤ ይልቁንም እየተጠናከረ የመጣው ዘመናዊው ቀኝ አገዛዝ የአፍሪካን ሕዝብ እያሰቃየ ነው ። እየ ተካሄደ ያለው ጨቋኝ አገዛዝ ያደረሰው ሰቆቃ በአኅጉሪቱ ሕዝቦች ጠን ካራ ትግል ይወገዳል ተብሎ ቢታመንበትም ፤ ችግሩን ያመጣው ማነው ? እንዴትስ ሊወገድ ይችላል ? ጨካኞቹ በጭካኔያቸው ሲገፉ ! እኛስ ምን ማድረግ አለብን ? እየተባለ በአኅጉሪቱ ሲቦካ የቆየውን አባባል እናት አፍሪካና የአፍሪካው ልጅ ያካሄዱትን ውይይት ከዚህ በታች በተገለጸው ግጥም ለማቅረብ እሞክራለሁ ፤ ይህንን ለማቅረብ ያስገደደኝ ትልቁ ምክ ንያት የሰው ልጅ ያለውን ሰፊ አእምሮ በአግባብ ያለመጠቀሙ ፤ ያም ማለት አንዱ ብልጥና ጀብደኛ በመሆን በሌላው ላይ ሲሰለጥን ፤ ሌላው ደግሞ ራሱን ዝቅ አድርጎ በመገመት ባርነትን በጸጋ መቀበል እንደሌለበት ከማሰብ ነው ። በዚህም ጨቋኞቹ እየፈጸሙት ያለው መሠሪ ተግባራቸው ትክክል እንዳልሆነ አውቀው ፤ ዓለም-አቀፋዊው ችግር እንዲወገድ የማድ ረግ ችሎታቸውን ቢያሳዩና ፤ የዕውቀታቸውን ፍሬ ፍጥረታት ሁሉ የሚጠ ቀሙበት ቢሆን ይበልጥ ይደነቁበታል እንጂ አንዳች የሚጎዱበት ነገር አይ ኖርምና ነው ። ምክንያቱም ዓለማችንን በጥበብ የሚያስተዳድራት አጣች እንጂ ለሁሉ የሚበቃ ሀብት አላጣችም ማለት ስለሚቻል !!!!!

ለፍጥረታት ሰላም የሚያስገኙ ጥበበኛ መሪዎችን አጣች እንጂ ፤ ዓለማችን ድሃ አይደለችም ስንል ሰዎች በግማሽ እንስሳዊ ባኅሪ በመነዳት ስግብግብነትን ራስ ወዳድነትን በማጠናከር ዓለማችንን የጦርነትና የኀማም መድረክ ለምን አደረጓት ? ለምን አላስተዋሉም ? ሥልጣኔስ በአመዛኙ ለልማት ነው ወይስ ለጥፋት ? ለየትኛው ነው ማገልገል ያለበት ? ያለ ጦርነት ፤ ያለ ዘረኝነት መኖር ሲቻል ለምን ይህን መልካም ሃሳብ ጠለቅ ብለው አላዩም ? ጠለቅ ብለው ማየት ቢሞክሩ ግን አንዱ ገፋፊ ፤ ሌላው ተገፋፊ የሚሆንበት ፤ ችግር ሳይኖር ችግር የሚፈበረክበት ፤ የሰው ልጅ ለጦርነት እልቂት የሚበቃበት ምክንያት አለመኖሩን መረዳት በቻሉ ነበር፡፡ ሰነፍ በስንፍናው ጣቶቹን ሲልስ ብልሁ ጥሮ መክበሩን ማንም ቀር እንደማይሰኝበት ሁሉ ፤ በዝርፊያ ፤ ደም በማፍሰስና የሰው ልጆችን ሕይወት በመቀሰፍ የሚፈጸመውን የወንጀል ክብ ረት ግን አብዛኛው የዓለማት ሕዝቦች የማይደግፉት ነው ።

የፈጣሪ ትዕዛዛትንም ብንመለከት ለጦርነት አይገፋፉንም ፤ ያም ሕግ ሠርተህ ጥረህ ግረህ ብላ ስለሚል ነው ። ግን ከፈጣሪ ሕግ ወጣ ያለው የዚህ የስግብ ግብነትና ራስ ወዳድነት ውጤት ፤ አንዱን የቢሊየነር ዶላር ባለቤት ሲያደር ገው ፤ ሌላው የሚልሰው የሚቀምሰውና ፤ ይልቁንም ከሰማይ ከሚወርደው ከምድር ከሚፈልቀው አንዲት ኩባያ ንጹህ ውሃ እንዲያጣ አድርጎታል ። በርግጥ የሰው ልብ ይህን አሰቃቂ ሕይወት በጭካኔ ሲመለከት ትክክል ነው ማለት እንችላለን ? በርግጥ የሰው አንጀት ይህን አሰቃቂ ሕይወት በጭካኔ ሲመለከት ትክክል ነው ማለት እንችላለን ? እንደዚያ የምንል አይመስለኝም ከተባለ ግን ሰፊውንና ብሩሁን የሰው ልጅ አዕምሮ ፤ ገና ጠልቀን ያልገባንበት መሆኑን ከማመላከት አልፎ አራዊተ-ኀሊና እንዳለን ያሳያል ማለት ይቻላል ።

የዚህን ታላቅ ጦስ ከአራት መቶ ዓመታት በላይ የተቀበለችው አፍሪካዊት ኮንትኔንት ስትሆን ፤ ዛሬም ችግሩ አልተወገደላትም ። ጨካኞችም በጭካኔያ ቸው እየተጠናከሩ ፤ ራሱን ሊከላከል ዕውቀት ያነሰውም ክፍል እርስ በርሱ እየተባላ ሁለቱም ጎራዎች ድንቁንና እጅግ የረቀቀ አዕምሯቸውን አልተጠቀ ሙበትም ። ለኔ እንደዚያ ነው የመሰለኝ !! ይህ ጽሁፍም ሆነ ግጥሙ ዕውነ ታን ቁልጭ አድርጎ በማሳየቱ በወንጀሉና የግፍ ሥራው የተጠናከሩ ኃይላት እንደማይቀበሉኝ !! ወይም ተደፍረናል እንደሚሉ አውቃለሁ ። ዳሩ ግን እኔ ይህንን መልዕክት ያቀረብሁት ዓለማችንንና ሕዝቦቹን ለሚወዱ አዳኞች እንጂ ለጦር አፍቃሪና ፤ ዓለማችንን ሲኦል እየከተቷት ላሉ ደም አፍሳሾች አይደለም ። እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ወደ ልና ድንቅ ሥራውን የምት ወዱ ብሩኅ አዕምሮ ያላችሁ ሁሉ ይህችን ዓለምና በላይዋ የሠፈሩትን ፍጥ

ረታት ሁሉ ታድኑ ዘንድ ነው ጥሪው ። ”change ” ለውጥ ብለን የለውጥን
አስፈላጊነት ከተስማማንበት ” yes we can !! ” አዎ ይቻላል !! ብለን ዓለማ
ችንን  ከጭለማ ወደ ብርሃን የማናመጣበት ምክንያት አይኖርምና ፣  እዚህ
ላይ ብንስማማ መልካም ይመስለኛል ። በነዚህ ድንቅና ብርቅዬ ቃላቶች ዓለ
ማችን ፕሬዚዳንት ኦባማን ተቀብላለችና በግሌ እጅግ አደንቃቸዋለሁ ።

አፍሪካዊያንም ጎልውናችንን እርቃኑን አስቀርተን ፣ በሰለጠነው ዘመን ውስጥ
እየ ኖርን ራሳችንን  ያለመግዛታችን ፣  በሃይማኖታዊና ጎሣዊ ስሜት ፣
ወይም አመለካከት  እርስ በርስ እየተባላን ከጊዜው ጋር  አለመራመዳችን ፣
ማንነታችንን ይልቁንም  የሰው ልጅነታችንን እያስጠቃን መሆኑ ተሰምቶን ራሳ
ችንን መለወጥ ያለመቻላችን ታላቅ ግምት ውስጥ እንደሚያስገባን ገና ግንዛቤ
የጨበጥን አይመስልም ፣  በዚህም ሌሎች ላይ የምንቀስረው ጣታችን ማጠር
ሊኖርበት ነው ። ይህንን ስል በቀድሚያ ከኋላ-ቀሩ አስተሳሰባችን እንድንወጣ
የራሳችንን ድርሻ አልከወንም ለማለት ነው ። ጆርጅ ኦርዌል ” animal farm ”
በተባለው ድንቅ መጽሐፉ የጠቃቀሳቸው እንስሳት ወይም አራዊት ፍጥረታት
ጠላታቸው ሰው መሆኑን አውቀው ፣ ብቀላ ማድረግ እንዳለባቸው የገለጹትን
ሲያሳይ ፣ ትልቁን አዕምሮ የተላበሰው የሰው ልጅ ግን ጠላት ወዳጁን ለይቶ
ያለማወቁ በእጅጉ ያሳዝነናል ! የዓለማችንን ትልቅ ኀመም በግልጽ ያስቀመጡ
ትና ፣  የፈጸሙት ተግባራት ቆጭቷቸው ዓለም-አቀፋዊ መተሳሰቦች ወደ ጥሩ
አቀጣጫ መቀየር እንዳለባቸው የገለጹት   ” John perkins ” – HIT MAN –
የተሰኘው መጽሐፋቸውን በጣም ነው ያደነቅሁላቸው ።  ራሱን መለወጥ የሚ
ፈልግ ሰው ሁሉ በኔ ግለሰባዊ ዕምነት የማደንቀው ነውና ሊደነቁ ይገባቸዋል ።
ከሳቸው አንፃር ደግሞ ዓለም-አቀፋዊ ስግብግብነትን በመሸፋፈን ለአፍሪካ ሕዝብ
የተስፋ ዳቦ በማስገመጥ ፣ ” The end of poverty ”  በሚል ያቀረቡት መጽሐፍ
ያልተስማማኝ   ” Jeffrey D . sachs ” ን  ጨርሶ አላደንቃቸውም ።  ባጠቃላይ
በጣም አወቅን የሚሉት ክፍሎች በአንድ ማርሽ ዓለምን እየረገጡ ለመኖር
የሚያስቡ ከሆነ ፣ ወይም ከዚህ ዛሬም እየታየ ካለው ብልሹና የሶስተኛውን
ዓለማት ሕዝቦች የማዳቀቅ ተግባሮቻቸው አልተናጠቡ ከሆነ ፣ ነገሩ አሳዛኝ
ከመሆኑ ባሻገር ፣ የዓለማት ችግር ቡሽ ላይ በተወረወሩት ጫማዎች ብቻ የሚ
ደመደም ሳይሆን ፣ ሕዝቦች የሚከባበሩበትን ዓለም-አቀፋዊ የፍቅርን ፣  የሰላ
ማዊ ግንኙነትን ድንበር ጥሶ የነሱንም በር የሚያንኳኳ ችግር የሚመጣ ስለ
ሚመስለኝ ፣ በውል ቢታሰብበት የተሻለ ይሆናል ።

በእርግጥ ዓለማችንን በጥበብ ማስተዳደር የሚችሉ መሪዎችን ገና ያለማግኘ
ታችን ጉዳይ በእጅጉ አሳሳቢ እንደመሆኑ ፣ በአሁኑ ወቅት ዓለማችን ሥርዓተ-
አልበኝነት ሰፍኖባት እንደ ጭራቅ የምታስፈራ፣ የምታስደነብር ፣ የምታስደነግጥ
መሆኗ ፣ እንዲያውም ሰው የራሱን ጥላ የሚፈራበት ወቅት ላይ መገኘታችን
ለዓለማችን በቅንነት የሚያስቡ መሪዎችን ካለመታደል ነውና፣ ነገሮችሊታረሙና
የሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት በአግባቡ ሊከበር ይገባዋል ። ዓለም-አቀፋዊው
ግንኙነት ጭለማ እየተላበሰ በመሆኑ ወደ ብርሃን ማምጣቱም ተገቢ ይሆናል ።
አጉል ብልጠትም ሆነ ፣ አጉል ጅልነት መጨረሻው ላይ ዓለም-አቀፋዊውን ተግ
ባብቶ የመኖር ባኅሪን ይጎዳዋል ያልሁት ፣ ያለምክንያት አይደለምና ፣ በእጅጉ
ሊታሰብበት ይገባል ለማለት ነው የዚህ ግጥም ዋና ተልዕኮው ። ይህንን ጽሁፍ
ያቀረብሁት ዓለማችን ላይ እየገዘፈ የመጣው የዲክታተሮች መበራከትና ሰብዓዊ
መብት ገፋፊነታቸው ፣ የአውዳሚ መሣሪያ ባለቤቶች መበራከት ፣ የዓየር ብክለ
ትና ሌሎችም የመንግሥታት አስተዳደራዊ ሥርዓቶች መዛባት አስፈሪነቱ ስለተ
ሰማኝና ፣ ከሰብዓዊነት በመነሳሳት በጥቅሉም ሲታይ ዓለም-አቀፋዊ ችግሮች
ከቁጥጥራችን ውጭ ስለሆኑና ከወዲሁ ልጓሙን ማጥበቅ መቻል አለበት ፣
በግፍና በከንቱ ልንጠፋፋም አይገባም ፣ አንዳችን ለአንዳችን እንዘን ፣ አንዳችን
አንዳችንን ከማታለል እንቆጠብና ዓለማችንን ከአጭበርባሪ ፕሮፓጋንዳ ፣ ከዘመ
ናዊው ቀኝ አገዛዝ ከዲክታተሮች አፈና ነፃ አድርገናት ፣ ሁላችንም እንደ
ባኅላዊ ዕምነታችን ፣ እንደ ፖለቲካዊ አመለካከታችን እንደ ብቃተ-ችሎታችን
ወዘተ...በሰላም መኖር ልንችል ይገባል ፣ ያለፈው ጭለማ አስተሳሰብ አይደገም
ለማለት ነው ። ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ይባል የለ !!!

## የአፍሪካ ልጅ ጥያቄ ፤

አዳምና ሄዋን እንደተፈጠሩባት ፤ ውቧ ገነትን መስለሽ !
እንደ ጃርት እሾህ በተጠቀጠቀው ደንሽ ተከበሽ
በባሕር በወንዞችሽ ፤ በሃይቆችና ተራሮችሽ አምረሽ
በመዓዛማው መልካም አየርሽ ታውደሽ !
በዱር አራዊትና ፤ በአዕዋፋቶችሽ ታጅበሽ
ከርሠ ማኅጸንሽ በደበቀው ፤ በማዕድን ሀብቶችሽ ኮርተሽ
ስስታም ነሽ !! ስስታም እልሻለሁ ባዕዳንን ብቻ ቀላቢ
ልጆችሽ የትም ወድቀን ፤ ሆነሻል የማደጎ ልጆች ሰብሳቢ !
በዓይኖቻችን ባላየነው በእጆቻችን ባልዳሰስነው
በመኖሩም ሳንጠቀም እንዲያው አለሽ በሚባለው
በማዕድኑ ሀብትሽ ከርሠ ማኅጸንሽ በደበቀው
የድሃ ቀብራራነትሽ
የሀብታምነት ጉስቁልናሽ
ገደቡ እስከመቼ ነው ?
ዳቦ አልባ ልጆችሽ በረሃብ ተሰቃይተው ሲያነቡ !
ባዕዳን በሀብትሽ ተንበሸብሸው ተትረፍርፏቸው ሲጠግቡ
በአኅጉራችን መድረሻ አጥተን ስንጉላላ !
የኢምፔሪያሊዝምን ጥይት ስንበላ
ታማኝ ባለአደራዬ ልጆቼ የምትያቸው
በባዕዳን የሚሾሙ ጠመንጃ ጥይት ጣኦታቸው !
ዘርፈው ያስዘርፉናል ሃፍረት አይሰማቸው
አደራሽን ያልጠበቁ ከሃዲና ሆዳም ናቸው !
መሪዎች የምትያቸው እንደ ከብት ይነዱናል
ይነዱናል..... ወዳሻቸው አቀጣጫ ይመሩናል !!!
በዘር በሃይማኖት ፤ በፖለቲካ ሽኩቻ ያቃውሱናል
ለዘለዓለም በማይገታ ጦርነት ውስጥ ይማግዱናል !
የኢምፔሪያሊዝምን ጥይት ዳቦ ነው ብለው ያበሉናል
ለመሃይምነት ፤ ለጎስቋላ ሕይወትና ለስደት ይዳርጉናል
ኅልውናችን ጨልሟል፤ የነፃነትን ብርሃን በዓለምሽ አላየ ንም
ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚጓዘው መከራ ዛሬም አልተወገደልንም
ዘመናት በጭለማ አልፈዋል ፤ መጪውንም አላወቅንም
በውል አትታዩንም አንቺም ጭለማ ለብሰሻል
እኛ ስንደነባበር ለኢምፔሪያሊዝም ብርሃን ሆነሻል !
በኃያላን ጭካኔ የበርካታ ትውልድ ደም በከንቱ ፈሷል
ደሙ አካልሽን አስቀጥቶ ልምላሜሽንም ኀድቶታል
እና አሁንም እመቤት ነኝ እያልሽ ትኩራሪያለሽ ?
ኢምፔሪያሊዝምን አጥግበሽ ልጆችሽን ታስርቢያለሽ ?

እስቲ ተጠየቂ አንቺ እማማ !
እስከ መቼ ነው ስቃያችን እስከ መቼ ነው የምንደማ ?
እስከ መቼ ነው የምንሰደድ እስከ መቼ ነው የምንጉላላ ?
እስከ መቼ እንናቃለን እስከ መቼ ነው የምንጠላ ?
ውሎ አድሮ ዝቃጭ ሕይወት ፤ እስከ መቼ ነው ባርነቱ ?
መኖርን እየረገምን የሞት ፍዳችን መብዛቱ ?
አንቺ የመሪዎችሽ ሆነሻል ፤ እኛ የመሪዎችሽ ተገዢ ፤
በእናት ጓዳችን አናዝ ይደሰት አንጂ ቀኝ ገዢ !
ታማኝ ባለአደራዬ መሪዎች የምትያቸው ፤
በባዕዳን የሚሾሙ ጠመንጃ ጥይት ጣኦታቸው ፤
ሰብዓዊነት–ዲሞክራሲ የተፋቸው !
ሕዝቦችሽን ለመምራት ብቃት ዕምነቱ የሌላቸው
አደራሽን ያልጠበቁ ከሃዲና ሆዳም ናቸው !
ሜዳውን እየሮጥን ፤ ተራራ ገደሉን ብንወጣና ብንወርድም ፤
ለነፃነት ብለን የፈለገውን መስዋዕትነት ብንከፍልም
የመኖር ነገር ሆኖ ፤ ለመኖር ስንል ብንደክምም ፤
አስመሳዩን ነው እንጂ ዕውነተኛውን ነፃነት አላየ ም !!

እስቲ ተጠየቂ ፣ ልጠየቅ በይ አንቺ እናት አፍሪካ
መቼ ይሆን ዕውነተኛውን ነፃነት ለብሰን በደስታ የምናወካ ?
በእናት ጓዳችን የምናዘው በጸጋሽ የምንመካ ?
በሆዳም መሪዎች ምትክ ዛቀኞችን የምንተካ ?
መቼ ይሆን የዲሞክራሲው ጮራ የሚፈነጥቅብን ?
መፈንጠቅም ብቻ ሳይሆን ፣
ሥሩ እንደ ሐረግ ተመዞ የሚያድግብን ?
አካል መንፈሳችን ሁሉ ፣ በዲሞክራሲ ጸዳል አምረውና አሸብርቀው
የተዘጋ ልሳናችን ተከፍቶ ፣ ዓይኖቻችን ከድንግዝግዝ ዓለም ተላቀው !
እጆችና እግሮቻችን ከዩዩአይ እግር ብረት ነፃ ወጥተው
የመናገር ፣ የመፃፍ ፣ የመሰብሰብ ነፃነታችንን ዕውነታ የምናየው
ለሰብዓዊ ክብራችን እርግጠኛውን ዋስትና የምናገኘው ?
መቼ ይሆን ጊዜያቱ እስቲ ንገሪን አንቺ እናት አፍሪካ
በልጆችሽ እንድትኮሪ በእናትነትሽ እንድንመካ ፣
ንገሪን ፣ ምከሪን ፣ ውቀሽን የምትይውንም እንሰማለን
ምክርሽን ተመርኩዘን ለአዲስ ሕይወት መሰናዶ እንጥራለን

## የእናት አፍሪካ መልስ !

እኔም ልውቀስዛ ልጄ ወቀሳዬ ቢገባህ......
ድክመትህን ልንገርዛ ! እናት አሰዳቢነትህ ቢሰማህ
አንተነትህን ለበታችነት ስሜት አጋልጠህ ለባዕዳን መስገድህን
ወዳጅ ጠላትህን የማትለይ ባርነት የማይመርህ መሆንህን
ኋላ-ቀሩ አጉል ባኅል በእግረ ሙቀ ቀፍድዶ አስሮዛል
አንድነትን ጠልተኸው ጠባብ ስሜትን አዳብረዛል
ወደኋላህ እየሄድህ ፣ የፊቱን ጉዞ ዘንግተዛል !
ኅልውናህንና ጥቁሩ ቀለምህን አስደፍረዛል
ስንፍና ወጥሮ ይዞዛል ፣ አርቆ ማሰብ ተስኖዛል
ዩዩና አይ ማለትም አንተና እኔ ነን ባዮቹ
ውስጥህ ገብተው ሲመቻቹ....
ኃይል ሁሉ የነሱ ሆኖ ሲያተራምሱህ.....
ማዕድኔን ጥሬ ሀብቴን ሁሉ ሲዘርፉ የጥይት ዳቦ ሲያጎርሱህ
በእናት አኅጉርህ የስደት ካምፕ ከፍተው ሲያጉሩህ!
እኔም በሮኬት ስቃጠል ስነድ ፣ ገላዬ በመድፍ ሲታረስ
የኬሚካል መቀበሪያ ሆኜ ተፈጥሮዬ ሲቃወስ
ገና አልነቃህም እኮ ልጄ ! የሕይወት ምንነት አልገባህ
የሥራን አኩሪነትና ፣ የሀገርን ልጅ ጥቅም አልተረዳህ
ከጥንታዊው አስተሳሰብ ፣ ከጎሣዊ ጠባብ ስሜት አልተላቀቅህ
ሁቱ ፣ ቱትሲ ፣ ኩኩዩ ፣ ካለንጂን......
አማራ ፣ አሮሞ ፣ ሐዊያ ፣ መጀርቲን...
አባምቦ ፣ ካባንጎ
ቺጋ ፣ ጊንዳ ፣ ሎንጎ
ሶጋ ፣ ጋንዳ ፣ ጊሱ
ማካንደ ፣ ዦሣ ፣ ዙሉ
ኒያምዌዚ ፣ ሱኩማ ፣ ቤና.....እየተባባልህ
በጎሠኝነት ተራርደህ.....
በድንቁርና አስተሳሰብ ተከፋፍለዛል !
ከሥልጣኔ እየራቅህ ....ሥልጡኖቹ ገዝተውዛል
በእርግጥ ተምሬያለሁ ብለዛል !
በዲፕሎምና በዲግሪ ተንበሽብሸዛል..... ግና !

ዕውቀት ችሎታህን አልቸርኸኝ ፣ የባዕድ አገልጋይ ሆነዛል !
ይህች ናት ችሎታ ! ይህች ናት ዕውቀት !!
የራስን ኅልውና አጥፍቶ ለሌሎች ኅልውና መሟገት !!
ዲግሪህን ተሸክመህ ወደ ሠለጠኑ ዓለማት ስትፈረጥጥ
በቁራሽ ዳቦ ተደልለህ ላያልፍልህ ስትጋጥጥ
ካገሩ የወጣ ሀገሩ እስኪመለስ....
ቢጭኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ !
እያልህ አንጎራጉር እንጂ ለኅልውናህ አልታገልህ !
እምቢ አሻፈረኝ ብለህ ለነፃነትህ አልተጋደልህ
ኃያላን እንዳንበሳ እያገሱ ሲያስፈራሩህ
ጎሠኝነትና የዛይማኖት ባላንጣነት ጠቃሚህ አስመስለው ሲሰብኩህ

በአጥፊ ፕሮፓጋንዳቸውና ፤ በፖለቲካ ውዝግብ ሲያናክሱህ

የጦር መሣሪያን በየቤትህ አድለው.....
ወገኖችህን ስታጠፉ ፤ ድል አድራጊ ነህ ብለው
ሲያጃጅሉህ ተጃጅለህ !!
ሲንቁህም ንቀትን አሜን ብለህ !
የጌታና የባሪያን ሥርዓት ለዘመናት አምነህ !!!
ስለ ኀልውናህ ፤ ስለ ኀልውናዬ መታገልን ዘንግተህ
በአስመሳይ ሹመታቸው ተኩራርተህ
ፑፔት ሆኖ መታዘዙ ሰብዓዊ ክብር ቢመስልህም
ጣዕርህን ማብዛት እንጂ ፤ ዘላቂ ሕይወት አይሆንህም
በዘመነ ሥልጣን ተውኔትህ ፤ ወገኖችህን ጨፍጭፊሃል !
ድፋው አዳፋው ፤ በቶርች ጥበሰው ብለሃል !
ይታሠር ፤ ይገረፍ ፤ ይሰቀል
ይሙት ብለህ በወገንህ ላይ ፈርደሃል ....
በሰብዓዊ መብት ገፈፋ ኃያላኖቹን ወክለሃል !
ነጩ ለነጭ ጥቅም ሲታገል
አንተ የጥቁር ወገኖችህን ጥቅም አጥፍተሃል...
ሰው ባገሩ እንዳይከበር ለስደት ሕይወት ዳርገሃል !
ሕፃናት ያለወላጅ ያላሳዳጊ መቅረታቸው አልቆጨህ
ድኩማንና አዛውንት ጧሪ በማጣታቸው አላዘንህ...
ብቻ ሆድ ይፍጀው !
ያቀጣጥለው ያንድደው ይፍጨው
ሆድ ይፍጀው እንጂ ሌላማ ምን ይባላል ?
ስለ ደካማ አስተሳሰብህ ቢፃፍ ቢነገርስ መቼ ያልቃል ?
ከስህተትህ አትማር ፤ ዓመታት ዘመናት አይለውጡህ !
በስንፍናህ አትቀጭ ውርደት ውድቀቱ አይሰለችህ !
ነጩ በኑሮው አድጎ ፤ ሰማየ-ሰማያት ሲመጥቅ !
ደልቶት አምሮበት ሲሞላቀቅ !
አንተም በምድራዊ ሲኦል የጣዕር ኑሮህ ስትጨነቅ ...
እና ! ምን እንድልህ ትሻለህ መከረኛዋ እናትህ ?
ለኔም ተቀማለህ ስል ፤ አንሰህ ስትገኝ ላንተነትህ !
ልፈር እንጂ ! አንተን ያፈራሁ ልከናነብ ውርደቴን
የሚፈርድልኝ ባይኖርም ዓለም ያውቀዋል ጭንቀቴን...
በኃያላን ወቃሽነት ....
በነሱው ከሳሽነት
በነሱው ዳኝነትና ፍርድ ሰጭነት
ሀብት ንብረቴን ሲዘርፉ.... !!
ልጆቼን በጥይትና በቶርች መሣሪያቸው ሲቀስፉ !!
ዓለሜን ዘዳርክ ኮንትኔንት እያሉ
በብርሃኔ ብርሃን ለብሰው ሲቀማጠሉ ....
ቀኝ ጉንጭህን ሲመቱ ፤ ግራውን ስትለግሥ !
ደደብነትህን አውቀዋል ፤ ለበቀል በቀል አትመልስ !
ሌዚ አፍሪካንስ እያሉ ሲያጥላሉህ
ሞራልህን አቃውሰው እንደ ፈረስ ሲጋልቡህ !
ሰብዕናህን ንቀውና አበሻቀጠውሃል ...
የዘመናት ባርነትን አጎናጽፈውሃል...
ሃሞትህ በውስጥህ ፈሶ የጀግንነት ወኔ ክዶሃል
በማዕቀብ ውሳኔ ተቀፍድዳችሁ ...
የገንዘባችሁ ጥንካሬ እንዲወድቅ ተገዳችሁ
ጥሬ ሀብታችሁ በነፃ ሲጋዝ ለነሱ
እናንተ በጎስቋላ ኑሮ ስትታመሱ....
የፍትሕ ያለ ብላችሁ !
ስትጮሁ ሰሚ አጥታችሁ !
በውል ተገንዝቤያለሁ ዓለማት እንደጨከኑባችሁ !!
በለምለሙ ገላዬ የሌለውን ባክቴሪያ አለ እያሉ
ኤቦላን ከወንዞቼ ፤ አድስን ከዝ ጀሮ መጣ እያሉ !
የባክቴሪያ ተሸካሚ አድርገውኛል ገዢዎቹ....
ከተኙበት ስላልነቁ ፤ ልጆቼ እንቅልፋሞቹ !
በብርሃኔ ተጠቀመውም ዘ ዳርክ ኮንትኔንት ማለታቸው
ጥቅሜን ንቀው አይደለም ፤ አንተን ነበር መስደባቸው

*የአዕምሮህን መጨለም ነበር የነገሩህ ! የሚነግሩህ !!*
*በጸጋዬ ጸጋ ለብሰህ መኖር አለመቻልህን ሲያበስሩህ*
*በሕይወትህ ጣልቃ ገብተው በፖለቲካ ሲያቋስሉህ*
*በጦር መሣሪያቸው ደም ሲያፋስሱህ !*
*የጥቁር ዘር ከሥቃይ እንዳይወጣ ነው ትግላቸው*
*መስገድ ማኅብደዱ ፤ ዘላለማዊ ባርነቱ ጥሚቸው !*
*ግና ! አሁንም ኋላቀሩን የጎሣ ፍልሚያህን ካልተውህ*
*የፖለቲካ ሽኩቻህን በመቻቻል ካላሣለፍህ*
*የጥቁርን ዘር ለማዳን ፤ እጅ ለእጅ ተያይዘህ ካልታገልህ*
*ነጭ ለነጭ እንደሚሚገት አንተም ለጥቁር ወገንህ ካልቆምህ*
*የጎሣና የአጉል ፖለቲከኛነት ዝቃጭ ወኔ....*
*ጦሱ ላንተ ብቻ ሳይሆን የሚተርፍ ነው ለኔ !!*
*ስለዚህ አሁን ከእንቅልፍህ ንቃ*
*የተኙትንም አንቃ ..... አነቃቃ !*
*ንቃ ቁም ተንቀሳቀስ አካባቢህን እየው*
*ስንፍናን ጥፋ በለው ፤ ወዳጅ ጠላትህንም ለየው*
*እኔ እንደማስተምርህ እንደምመክርህ ካስተዋልኸው*
*የሚጠላህን ጥላ የሚወድህን ውደደው ፤*
*ጥቁር ቀለምህን አስከብር የሚንቅህን ናቀው ፤*
*እኔ እናታችሁ የጥቁር ሕዝብ ዓለም ነኝ !*
*ልጆቼ ጠንክሩ እንጂ ፤ የተትረፈረፈ ሀብት አለኝ ፤*
*ሥርዓትን አልጠላም ፤ ሥርዓትን አስከብሩ ፤*
*በፈለጋችሁበትም ሥፈሩ ፤ የፈለጋችሁበትም ኑሩ ፤*
*ቀለሙ ቀለሜ የሆነው ጥቁሩ ልጄ በሩ አይዘጋበት ፤*
*ከየት መጣህ ? የት ትሄዳለህ ሳይባል በጉያዬ ይኑርበት !*
*አውሮፓ የነጮች እናት ስትሆን ፤ እኔም የጥቁሮች እናት ነኝ !*
*ልጆቼ ነቀታችሁ ብትደራጁ ከቶ ማነው የሚደፍረኝ ?*
*ጥቁር በጥቁር ተጣልታችሁ ለጠላቶች በር አትክፈቱ ፤*
*አደንቋሪ ገዥዎችን ተፋለሙ ፤ ስለ ነፃነታችሁ ተሟገቱ ...*
*ካለፈው ችግራችሁ ተማሩ ፤ የነቃችሁ የተጠናከራችሁ ሁኑ !*
*እንግዲህ ይብቃህ ልጄ ፤ ከድንግዝግዙ ዓለም ተላቀቅ !*
*የጥቁርን ዘር አስከብር ፤ ከዲሞክራሲም ጋር ተዋወቅ ፤*
*ለቁስሌ ፈውስ ለሕመሜም መድኅን ብትሆነኝ ፤*
*እኔም ቃል እገባልሃለሁ ፤ ቃሌ ፍጹም ነው እመነኝ !*
*በጸጋዬ የማኮራህ ፤ በብርሃኔ ብርሃን የማሳይህ እናትህ ነኝ!*
*እመነኝ እናትህ ነኝ ! እመነኝ እናትህ ነኝ !*

<u>*ደራሲው መለኮት ባዩህ*</u>